# የአቶ መለስ ሁለት ነብሶች፤
# አንዱ የምታጣጥር ሌላዋ የሞተች

አሥራደው (ከፈረንሳይ)



- « የብሄር ብሄረሰቦች እኩልነት፤ የራስን እድል በራስ መወሰን እስከመገንጠል !
- ጨርቅ ሳይሆን ወርቅ ከሆነው ከትግራይ ሕዝብ በመፈጠሬ እኮራለሁ !
- የኢትዮጵያ ባንዲራ ጨርቅ ነው !
- የአድዋ ድል ለደቡቡ ምኑ ነው !
- ኢንተርሃምዌ
- ተራ ቦዘኔ !
- ባለ ሁለት አሃዝ ዕድገት አስመዝገበናል፤
- እድገትና ትራንስፎርሜሽን !
- አውራ ፓርቲ !
- መተካካት፤
- ልማታዊ መንግሥት፤
- የአባይ ህዳሴ ግድብ፤
- ከነጮች ቃል በቃል የተገለበጠ የሽብርተኛ ህግ ነው ያወጣነው፤
- ሕገ መንግሥቱን ለመናድ የተነሱ ነውጠኞች፤
- ነጭ ለባሽ
- የሻ'ቢያ ተላላኪዎች
- ገበሬው ሚሌንየር ሆኗል !
- አኬልዳማ........ወዘተ »

እንደ ሕዝቡ ሞትንም ልሸውደው ሞክሬ፤ እሱ ግን ነቃብኝ !

*« Mentir est un métier*
*Démentir c'est tout un art »*
*Volinski*

*« መዋሸት ሞያ ነው*
*ውሸትን ማጋለጥ ደግም ትልቅ ጥበብ ነው »*
*ቮለንስኪ*

*ከዚህ በላይ የጠቃቀስኳቸው፤ አቶ መለስ ዜናዊ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የተጫወቷቸው የቁማር ጨዋታዎች ሲሆኑ፤*
*በዚህ የቁማር ጨወታ ተጠቃሚ የሆኑ ጥቂት ሆድ አደሮች ቢኖሩም፤ ብዙ የተጎዱ ዜጎች ለመኖራቸው ደግም አሌ አይባልም ::*

*አንዲት ዕውነት የተራበች ነብስ ብዙ ዕውነት የተራቡ ወገኖቿን ነብሶች ለመታደግ የምታደርገው የሃቅ ጩኸት፤ የጥቂት ጠግቦ አደር ነብሶችን ሠላም ነስታ ታሸብራለች:: እየተኙ እንቅልፍ የላቸውም፤ ቢተኙም አብዛኛው በቅዠት የተሞላ ነው፤ እየበሉ አካላቸው ቢደልብም፤ የሕሊናቸው መክሳት ያሳብቅባቸዋል፤ አይምሯቸው ባዶ በመሆኑ ወና ወና ይሸታል፤ ልባቸው በቂም ስለተሞላ፤ የሚረጨው ፍቅር ሳይሆን ጥላቻን ነው፤ ሆዳቸው ዘወትር እህል ቢያስተናግድም፤ ከተራበው ወገናቸው በበለጠ እየበሉም ይርባቸዋል፤ አንጀታቸው ለድሃ ወገኖቻቸው የሚያዝንበት ነቁጥ ታህል ሥፍራ የለውም፤ ጣቶቻቸው ብዕር ከመጨበጥ ይልቅ የጠመንጃ ቃታ ለመሳብ ይፈጥናሉ፤ ብዕርን በብዕር የመሞገት ባሕል ስሌላቸው ብዕርን በጥይት ለመርታት ይመርጣሉ ::*

- *እስክንድር ነጋ ወሕኒቤት በተወለደ ልጁ ዕንባ እያጠቀሰ የጻፈው ዕውነትን ነው ፤*
- *አንዱዓለም አራጌ ለሆዱ ከማደር ይልቅ፤ ለሕሊናው በማደሩ ነው የታሰረው፤*
- *ርዕዮት ዓለሙ በተሸከመችው የውሃ እንስራ ሙሉ፤ ቀለም በጥብጣ ሃቅን ስለጻፈች ነው ያሰሯት፤*
- *ተመስገን ደሳለኝ ለፍትህ የበላይነት ስለጮኸ ነው ያሰሩት........ ወዘተ.*
- *ተመስገን ሲታሰር የፍትህ አምደኞችም አብረው የሕሊና እስረኞች ሆነዋል፤*
- *ተመስገን ሲታሰር የፍትህ አንባቢዎችም በሙሉ አብረው ታስረዋል፤*
- *እኔም ይችን የወገኖቼን ሲቃ የምትናገር ጽሑፍ በመጨንቆሬ እስረኛ ነኝ፤*
- *እናም ሁላችንም ሽብርተኞች ነን (በእነሱ አባባልና ድርጊት)፤*
- *አዎ ፍትህ በመጥፋቷ ሁላችንም እስረኞች ነን፤ በመሆኑም የኢትዮጵያ ሕዝብ በሙሉ ታስሯል ::*

*እነሱም እራሳቸው በተኮሱት ጥይት ተደናግጠው እየተሸበሩ፤ በማሸበር፤ የሚይዙትና የሚለቁት ጠፍቷቸው ብቻቸውን ላለመውደቅ ሳር ቅጠሉን እየቧጠጡ ከውዲያ ወዲህ ይወራጨሉ፤ መካሪዎቻቸውም ሽር ጉድ ይላሉ፤ ሕዝቡም አድፍጦ ኮሽ የሚል ነገር ይጠብቃል፤ እግዚአብሔር የጀመረውን ሥራ የመጨረስ ግዴታ አለበት:: « ወጥተህ ወርደህ የላብህን ወዝ ትበላለህ » ባለው መሠረት፤ ሁሉን ከእግዚአብሔር መጠበቅ፤ በፈጣሪው አምሳል የመፈጠሩን ክብር ዝቅ ስለሚያደርግበት፤ የፈጠረለትን አእምሮ መጠቀም የግድ ይለዋል::*

ዕውነት በተነገራቸው ቁጥር፤ ሃቁን የነገሯቸውን ሁሉ ሽብርተኛ እያሉ ለሚያስሩ ተሸባሪዎች፤ ዕውነትን ለመዋጥ በስብ የተደፈነው ጉሮሯቸው እየተናነቀ ቢያስቸግራቸውም ሃቁን እየነገርናቸው እራሳቸው በጣዱት፤ የጥላቻና የሽብር ብረት ድስት ውስጥ እየተንፈቀፈቁ ፈልተው እንዲተኑ ከማድረግ አንቆጠብም ::

የኛ መሳሪያ ሃቅና ብዕር እንጂ እንደነሱ ጠብመንጃና ጥይት አይደለም፤ የኛ ልብ ፍቅርን እንጂ እንደነሱ ልብ ጥላቻን አይረጭም፤ እኛ አንድነት፤ እኩልነት፤ ወንድማማችነትና ሠላምን ለሕዝባችን እንመኛለን እንጂ፤ እንደነሱ በዘር፤ በሃይማኖት፤ በጎሳና በጎጥ ከፋፍለን ሕዝብን አናባላም፤ አገር አንበታትንም ::

እኛ በሥጋችን ያልደላን ሰዎች የፈጣሪን (የእግዚአብሔርን) ድርሻ ወስደን፤ በነብሰ የዳኝነት ወንበር ላይ ቂጢጥ ብለን፤ የእከሌን ነብስ ይማር፤ የእከሌ ነብስ አይማር ብለን ፍርድ ለመስጠት ብቃት፤ ዕውቀትና ቅድስናው ስለሌለን ፍርዱን ለፈጣሪ ትተናል::
እግዚአብሔር የድርሻውን እየሠራ ነው፤ የቀረው የኛ የሰዎቹ ድርሻ ነው፤ የኛንም ድርሻ እግዚአብሔር እንዲሠራልን እጃችንን አጣምረን የምንጠብቅ ከሆነ በስንፍናችን ይቀጣናል፤ ቅጣቱም እጅግ የከፋ ይሆናል:: የመረረ ሕይወትን የምንገላገልበትና ከቁም እስር የምንወጣበት ጊዜው አሁን መሆኑን አብስሮናል፤ ሁላችንም የዜግነት ድርሻችንን በመወጣት ያለውን አስከፊ ሁኔታ የመለወጫው ጊዜ አሁን ነው:: ከአሁን በኋላ ከጨለመ ተመልሶ አይነጋም::
ተመስገን ደሳለኝም ያለው ይኸንኑ ነው፤ « እኔ የምችለውን አድርጌያለሁ የቀረው የሕዝብ ፋንታ ነው » ብሎ ምኞቱንና ማሳሰቢያውንም ትቶልን ታስሯል ::
ታዲያ ሕዝቡ ድርሻውን ለመወጣት የሚጠብቀው ምንድነው ?

የአቶ መለስ ዜናዊ ነብስና፤ አቶ መለስ ዜናዊ በአጋዚ ሠራዊታቸው ያስፈጇቸው፤ ወንድሞቻችንና እህቶቻችን፤ ነብሶች፤ በፈጣሪ የፍርድ ሚዛን ላይ ሲመዘኑ፤ የትኛው እንደ ዶሮ ላባ እንደሚቀል? የትኛው እንደብረት እንደሚከብድ? የመንግሥተ ሰማያት በር ለማን ወልል ብሎ እንደሚከፈት? የመንግሥተ ሰማያት በርና መስኮት በማን ላይ ክርችም ብለው እንደሚዘጋ? የአንድዬ ፋንታ ነው :: ወሬ በቃ ለተግባር እንነሳ! አቶ መለስ ዜናዊ፤ በአጋዚ ሠራዊታቸው ያስጨረሷቸው ወገኖቻችንን ቤተሰቦች እንባ የምናብሰበት ጊዜው አሁን ነው፤ እነሱን የምንክሳቸው ለሞቱበት አላማ በመቆም፤ በመቃብራቸው ላይ የዲሞክራሲን ሰንደቅ ስናውለበልብ ብቻ ነው፤ እናም ጊዜው አሁን ነው !

በእርገጠኝነት መናገር የሚቻለው፤ በአቶ መለስ ዜናዊ ሞት፤ የሚድኑ ነብሶች እንዳሉ ሁሉ፤ በአቶ መለስ ዜናዊ ሞት፤ የሚሞቱ ነብሶችም ይኖራሉ:: ግን ግዴለም፤ ለፍርድ አንቸኩል፤ ደግሞስ ማን ፈራጅ አድርጎን ?

ነገር ግን፤ በርሃብና በችጋር ከተጎሳቆለው ሰውነታችን፤ ለአቶ መለስ ዜናዊ ለቅሶ የምናዋጣው የዕንባ ጎርፍ፤ ከጨሰው ኑሮ ተርፎን የምናዋጣው ገንዘብ የለንም::

*በበላ አንጀታቸው የሳቸው ሹመኞች፤ በጋን የሚቀዳ ዕንባ እያፈሰሱ፤ የሳቸው ልማታዊ ሌቦች፤ ከዘረፋት የሕዝብ ሃብት እየገመሱ አዋጥተው ይሸኟቸው።*
*ለቀብሩ የደረቀ ሰውነታችን፤ ለአርባና ለተዝካሩም አይወዛምና፤ ከወዲሁ ከጠወለገው ሰውነታችን የሚፈልቅ የእንባ ምንጭ፤ ከተራቆተው ኪሳችን የሚዋጣ ሳንቲም የለምና አስቡበት ።*
***የቄሳርን ለቄሳር፤ የሕዝቡን ለእግዚአብሔር፤ እግዚአብሔርም ለሕዝቡ፤ ሕዝብም ለአገሩ፤ ብለናልና !***

*ከንግዲህ ላልደላን፤ ላልተመቸንና እያሳመመን ላለው ምድራዊ ኑሯችን አብረን መፍትሄ እናፈላልግ። (እዚህ ላይ ከመንግሥተ ሰማያቱ ይልቅ የምድራዊው ኑሮ ይበልጣል ለማለት እንዳልዳዳኝ ተረዱኝ) ብዙው ወገናችን እየተራበ፤ እየተራቆተ፤ እየተሰቃየ፤ እየታሰረ፤ እየተሰደደ፤ እየሞተ.........ወዘተ ነውና !*

*የሞተችው የአቶ መለሰ ዜናዊ ነብስ ገና ወደ መሄጃዋ አልተሳፈረችም፤ ሆኖም የምታጣጥረው ሁለተኛዋ የአቶ መለሰ ነብስ ደግሞ፤ በአቶ በረከት ስምኦንና በመሰሎቻቸው አካል ላይ ተጻራ፤ (ተጣብቃ) « ምንም የሚለወጥ ነገር የለም፤ እኛ ህውሃቶች ኃይለማርያም ደሳለኝን የጋሪ ፈረስ አድርገን እየጋለብነው፤ መተካካት በሚለው ስልታችን ሥርአቱ እንዳለ ይቀጥላል» ብለውናል።*

*እናም፤*
*መራቡ ይቀጥላል !*
*የኑሮ ውድነቱም ይቀጥላል !*
*መታሰሩም ይቀጥላል !*
*መሰደዱም ይቀጥላል !*
*መገደሉም ይቀጥላል !*
*መዘረፉም ይቀጥላል !*
*መታፈኑም ይቀጥላል !.........ሁሉም ይቀጥላል ብለውናል ! !*

*እነዚህ ከአገራቸው ጥቅም፤ ክብርና ልዕልና ይልቅ፤ ለነጮች ጥቅም ዘብ የቆሙ፤ በሙስና (በንቅዘት) ተደፍቀው፤ የአገራቸውን ሃብት እየዘረፉ በባዕድ ባንክ የሚከምሩ፤ ሕዝባቸውን እያስራቡ፤ ለቻይና፤ ለሕድና ለአረብ አገሮች መሬቱን በመቸርቸር፤ ሕዝቡን እያስራቡ የሰንዴ መለመኛ ያደረጉ፤*
*የሕዝባቸውን የማሰብ፤ የመጻፍ፤ የመናገር፤ የመሰብሰብና የመደራጀት መብት የገፈፉ፤ ወጣቱን ትውልድ ለሰደት፤ ለሥራ አጥነት፤ ለዘማዊነትና ለመጥፎ ልምድ የዳረጉ፤ ሕዝባቸውን ነፃነት ገፈው፤ ለባርነት፤ ለበታችነትና ለዝቅተኝነት የዳረጉ.........ወዘተ የአገራቸው ጡት ነካሾችን፤ ሕዝቡ ከእንግዲህ በቃ ! ሊላቸው ይገባል ።*

*በመተማመን ተባብሮ የተነሳ ሕዝብ ያሸንፋል !!*
*ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ !*
*እግዚአብሔር ኢትዮጵያንና ሕዝቧን ይባርክ !*
*ነሃሴ 20 ቀን 2004 ዓ.ም. (August 26/ 2012 )*